የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ — ታኅሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 10
ADDIS ABABA - 12th Dec. 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፶፫/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኦፔክ ዓለም አቀፍ የልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........ ገጽ ፪፻፺

## CONTENTS

Proclamation No. 53/1996
Opec Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Teacher Training Institutes Project Ratification Proclamation ........ Page 290

## አዋጅ ቁጥር ፶፫/፲፱፻፹፱

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ዓለም አቀፍ የልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፯ ሚሊዮን (ሰባት ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ዓለም አቀፍ የልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፮ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ ፡

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኦፔክ ዓለም አቀፍ የልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፶፫/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 53/1996

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

*WHEREAS*, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Opec Fund for International Development stipulating that the Opec Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 7,000,000 USD (Seven Million United States Dollars) for Financing the Teacher Training Institutes Project was signed in Addis Ababa on the 15th day of July, 1996;

*WHEREAS*, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 12th day of December, 1996;

*NOW, THEREFORE*, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Opec Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Teacher Training Institutes Project Ratification Proclamation No. 53/1996."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 1·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ዓለም አቀፍ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ጁላይ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፮ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር ፮፻፶፱P የብድር ስምምነት ነው ።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፯ ሚሊዮን (ሰባት ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 659P signed in Addis Ababa, on the 15th day of July 1996 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Opec Fund for International Development.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minsiter of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 7,000,000 USD (Seven Million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 12th day of December, 1996.

Done at Addis Ababa, this 12th of December, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA



ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE